በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

*የተሰጠ መግለጫ*

*ሕዳር 9 ቀን 2011ዓ.ም*

# *ማህበራት ይፈቱ፤*
# *የችግሮች ሁሉ ዋናው ምንጭ የጎሳ ፖለቲካ ነው!!!*

*በአገራችን በኢትዮጵያ ሠፍኖ ላለውፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ምክኒያቱ የወያኔ መንግስት ሥልጣን ከወጣ ጀምሮ እያራመደ ያለው የጎሳ ፖለቲካ ነው። ይኸው የጎሳ ፖለቲካ የትምህርቱን ዘርፍ በከፍተኛ ሁኔታ የጎዳው ብቻ ሳይሆን ምስቅልቅሉ እንዲወጣ በማድረግ የትምህርቱ ጥራት ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁልቁል እንዲወርድ አድርጓል።*

*በአሁኑ ሰዓት ከምንጊዜውም በባሰ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ለዘመናት ከኖሩበት ሥፍራ እንዲፈናቀሉ ተደርገዋል፣ተገድለዋል፣ ንብረታቸውም ተዘርፏል። የዚህ ሁሉ መዘዝ የወያኔ የጎሳ ፖለቲካ አደረጃጀት ነው። በህዝብ ላይ የሚደርሰው መፈናቀልና በትምህርቱ ሂደት ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት ይህ መግለጫ እስከወጣ ድረስ እንደቀጠለ ነው።*

*ከዚህ አንፃር ሕዳር 1985 ዓም እ.ኢ.አ የወያኔ አገዛዝ ጎሳን መሰረት ያደረገ የማህበራት አደረጃጀት ተግባራዊ ለማድረግ አቅዶ መምህራንን በጎሣ በመከፋፈል የዚህ የዚያ ጎሳ መምህራን ማህበር በማለትና የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ባለመሆናችሁ አካባቢውን እንዲለቁና እንዲወጡ አድርጓል። መምህራን በመረጡበት አካባቢ የመኖርና የመስራት የዜግነት መብታቸው እንዲገፈፍ ተደርጓል። ብዙ የተማረ የሰው ኃይልና ጉልበት እንዲሁም ገንዘብ ያለአግባብ እንዲባክን ሆኗል። በዚህ ወቅት ነበር የካቲት 1985ዓም እ.ኢ.አ 14ኛው የኢመማ ጉባኤ ተካሂዶ የማህበሩ ቋሚ አመራር የተሰየመው። አዲሱ የማህበሩ አመራርና የጉባኤው ተሳታፊዎች የወያኔ አገዛዝ ( በወቅቱ የሽግግር መንግስት ተብሎ የሚጠራው) በኢመማ ላይ የሚያደርገውን ጣልቃገቢነት በመቃወም፣ መምህራንን በጎሳ ማደራጀቱ እንዲገታ፣ የመምህራን የዜግነት መብታቸው እንዲከበር፣ ከስራቸው የማባረርና የማፈናቀሉ ድርጊት እንዲቆም በሰላማዊ ስልፍ ጠየቁ። ወያኔ በመምህራን በኩል ለቀረቡት አግባቢነት ለነበራቸው ጥያቄዎች መልስ ከመስጠት ይልቅ ማህበሩን ለማፍረስ ቆርጦ ተነሣ።*

*ይህች ባቂላ ካደረች አትቆረጠምም፤ የደርግን ሰራዊት ከመበተን በፊት መበተን ያለበት ኢመማ ነው በማለት ወያኔ መጋቢት ወር 1985ዓም እ.ኢ.አ በየክልሉ ካስፈራቸው የኮር አባላት መካከል መምህራን እንደሆኑ በማስመሰል በአዲስ አበባ በያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ውስጥ በመሰባሰብ የሸእቢያ ወኪል በሆነው በዮሐንስ ሐጎስ የሚመራ ተለጣፊ ማህበር አቋቋመ።ይህ ተለጣፊ ማህበር በኢመማ ስም በመንቀሳቀስ መምህራን በየጊዜው የሚያነሱትን የመበት ጥያቄዎች ተሰሚነት እንዳያገኙ ለማድረግ ከስርዓቱ ጋር አብሮ ሰርቷል።የመምህራንን የስራ ማቆም አድማዎችን ተቃውሟል። መምህራን ከስራቸው ሲባረሩ አይቶ እንደላያ ሆኗል። ከስርዓቱ ጎን በመቆም መምህራንን ሲያጠቃ ቆይቷል። በዚህም የተነሳ መምህራን በተለያዩ ጊዜና በተለያዩ ስብሰባዎች ተለጣፊው ማህበር እንደማይወክላቸው ገጸዋል፣ አጋልጠዋል። ማህበሩ እንዲፈርስም ታግለዋል፣ በመታገል ላይ ናቸው።*

*የወያኔ የጎሣ ፖለቲካ አደረጃጀት በዚህ ሳያበቃ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ፣ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች የሚማሩ ተማሪዎችን በየጎሳቸው እንዲደራጁ አድርጓል።በዚህም የተነሳ የተማሪዎች አንድነት እንዳይኖር ያስተሳሰራቸው ኢትዮጵያዊ ክር እንዲላላ፣ ኢትዮጵያዊነት እንዲደበዝዝና የተማሪዎች የጋራ መሰብሰቢያ ማዕከሎች እንዳኖሩ በማድረግ ጎሣኝነትና ጥላቻ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ሳያሳልስ በእጅጉ ሰርቷል። በአሁኑ ሰዓት የጎሳ ፖለቲካ ባመጠው ጣጣና መዘዝ የተነሳ -ለሕልውናችን አስጊ ሁኔታ በመፈጠሩ በክልላችን ባሉ ዩኒቨርስቲዎች እንደንመደብ ይደረግ የሚል አሳፋሪ ጥያቄ ካንዳንድ ክልል ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እየተደመጠ ነው።*

*በሌላ በኩል በ1984ዓም እ.ኢ.አ በመላ አገሪቱ የሚገኙ መምህራን ያነሷቸውን ዋና ዋና የኢኮኖሚና የመብት ጥያቄዎች በወቅቱ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ በ20 ጥያቄዎች አካቶ ነሐሴ ወር 1984 ዓም በወያኔ ለተቋቋመው የሽግግር መንግስት ማቅረቡ ይታወቃል።ከጥያቄዎቹ በ2ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጻፈውን እንጠቅሳለን <<**ህብረተሰቡና መንግስት ለትምህርት ግምት ተገቢውን ቦታ እንዲይዝ ከፍተኛ ትኩረት ተደርጎበት የአገራችን የትምህርት ፖሊሲ አነዳደፍ በጥናትና በምርምር ላይ የተመሰረተ፣በአዘጋጃጀቱም ከአንድ ወገን ወይም ቡድን የፖለቲካ ተጽእኖ የጸዳና ከሁሉም በላይ የሕዝቡን ፍላጎት የሚያሟላ በቀጥታ ብቃት ባላቸውና የሙያው ባለቤት በሆኑ መምህራን ፣ ወላጆችና ተማሪዎች ባሳተፈ መልክ እንዲሆን** >> የሚል ነው። ነገር ግን ይህን የመህራንን ጥያቄ የወያኔ አገዛዝ ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት ፤ ባለድርሻ አካላትን በማግለል<< ለብሔር -ብሔረሰቦች ተደራሽ የሆነ የሊቃውንት ማፍሪያ ነው >> በሚል በዓልም አቀፍ የገንዘብ አበዳሪ ድርጅትና በዓለም ባንክ እስፖንሰርነት ጎሳን መሰረት ያደረገ << አዲስ የትምህርት ስልጠና>> በሚል በ1986 ዓም ኢ.ኢ.አየትምህርት ፖሊሲውን ተግባራዊ አደረገ። ይኸው የት/ ፖሊሲ ውሎ ሣያድር ትውልድ ገዳይ እንደሆነ፤*

P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

*ውጤቱም የትምህርቱን ጥራት ቀድሞ ከነበረው በባሰ ሁኔታ አዘቅት ከተተው። የኋላ ኋላ የስርዓቱ መሪዎች ሳይቀሩ ትውልድ ገዳይነቱን ለማመን ተገደዋል።አሁንም በተመሳሳይ መንገድ የትምህርትና የስልጠና ችግሮቻችንና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን የያዘ 84 ገጾች ያሉት የፍኖተ ከርታ በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት እስትራቴጂ ማእከል መሰናዳቱን የትምህርት ሚኒስቴር ገልጿል። ይሄው በትምህርት ሚኒስቴር ይፋ የሆነው የትምህርት ፍኖተ ካርታ በ1986ዓም ተግባራዊ ከሆነው ትውልድ ገዳይ የትምህርት ፖሊሲ የተለየ አይደለም። በአዘጋጃጀቱም ሆነ በአሰራሩ ያው አንደቀድሞው ሆኖ ቀጣዩን ትውልድ የሚገድል ነው። <u>ታዲያ ምን መደረግ አለበት?</u>*

*በቅድሚያ መምህራን ማህበራቸውን ኢመማ ከእስር እንዲፈታ መጠየቅ ይጠበቅብናል። አሁን ያለው ተለጣፊ ማህበር የስርዓቱ አገልጋይ ስለሆነ በአስቸኳይ ተወግዶ በምትኩ በመምህራን ለመምህራን የሆነውን ማህበራችንን ኢመማን ከመንግስትም ሆነ ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ጣልቃገቢነት ነፃ በሆነ መንገድ ከታች ወደ ላይ ማለትም ከትምህርት ቤት መሰረታዊ ማህበር አስከ አገር አቀፍ መምህራን ማህበር ድረስ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ማዋቀር፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎች የሲቪል ማህበራት የሠራተኞች ማህበርን ጨምሮ ከእስር እንዲፈቱና በአባላት ነፃ ፍላጎት እንዲቋቋሙ ለማድረግ ትብብር ማድረግ፤ በመቀጠልም እየተዘጋጀ ያለው የትምህር የፍኖተ ካርታ ባለድርሻ አካላትን ያላከተተና አዘጋጃጀቱም ያው እንደቀድሞው ስለሆነ አገር በቀልና ህዝባዊ እንዲሆን የትምህርት ፖሊሲው በባለድርሻ አካላት አማካኝነት እንዲዘጋጅ ለተግባራዊነቱም መምህራን፣ ወላጆች፣ ተማሪዎች እንዲሁም ከትምህርቱ ተጠቃሚ የሚሆነው ሕዝብ እንዲታገሉ በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ጥሪ ያቀርባል። ይህ ተግባር ስራ ላይ የሚውልበት ወቅት ነው ብሎም ያምናል።በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አስተባባሪ ኮሚቴ በአርባ ምንጭ ከተማ ውስጥ በሚገኙ 50 ት/ቤቶች የሚያስተምሩ 860 መምህራን ለአባይ ግድብ ያዋጡት 30 ሚሊዮን ብር እንዲመለስላቸው ጠይቀው ባለማግኘታቸው ከጥቅምት 20 ቀን ጀምሮ የስራ ማቆም አድማ ማድረጋቸውን ይደግፋል። ገንዘቡም ለመምህራኑ እንዲመለስ ይጠይቃል፤ ከጎናቸውም ይቆማል።*

*በእጠቃላይ በአግራችን ለሚታዩት ውስብስብ ችግሮች በዋነኛነት መንስኤው የጎሣ ፖለቲካ ስለሆነ ይህው የዘርና የጎሣ ፖለቲካ እንዲወገድ፣ ስርዓተ አልባኝነት እንዲጠፋ፣ የህግ የበላይነት እንዲሰፍን፣የኢትዮጵያ ሕዝብ ባጣቃላይና መምህራን በተለይ የጀመሩትን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እንዲቀጥሉ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ይጠይቃል።*

*ማህበራት ከእስር ይፈቱ!!*
*ለትምህርት ጥራት አገር በቀል ሕዝባዊ የትምህርት ፖሊሲ !!*
*የሕግ የበላይነት ይስፈን!!*